# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)

## Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

### ያለ ነፃ ፕሬስ ዴሞክራሲ የሚታሰብ አይሆንም!!

ሚያዝያ 25 ቀን 2002 ዓ.ም

በየዓመቱ ሚያዝያ 25 (ሜይ 3) ዓለም አቀፍ የፕሬስ ነፃነት ቀን በነፃው ፕሬስ አባላት፤ ለሰብዓዊ መብት ጥበቃ በቆሙ ሰላም ወዳዶች፥ በተለያዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የተለያዩ መግለጫዎችን በማውጣት፣ ፊልሞችንና ትርኢቶችን ለሕዝብ በማሳየት ያከብሩታል። ይህም ያለ ምክንያት አይደለም። ነፃና ከጥገኝነት የተላቀቀ መድበላዊነትን የተላበሰ ፕሬስ መኖር ለአንድ ሕብረተሰብ ለዴሞክራሲ፣ ለኤኮኖሚ እድገትና ልማት መገኘት ዋና መሰረት በመሆኑ ነው። የሃሳብ ነፃነትና የግለሰብ ነፃነት የሚነጣጠሉ ሳይሆኑ በአንድነት ተቆላልፈው የሚገኙ ናቸው። የግለሰብ ነፃነት ሳይከበር የሀሳብ ነፃነት ተግባራዊ ሊሆን ጨርሶ አይችልም። ስለሆነም ማንኛውም ጋዜጠኛ በየትኛውም ሀገር ሙያውን ተግባራዊ በሚያደርግበት ወቅት መታሰር፡ መንገላታት፡ በፍርሃት ሰቀቀን መታወክ ወይንም ደግሞ ሕይወቱ ለአደጋ መጋለጥ ግለሰባዊ መብትን መጣስ ነውና አንጥብቆ ማውገዝ አስፈላጊና አግባብነትም ያለው ነው።

ነገር ግን በአሁኑ ወቅት ይህ ግንዛቤ ተቀባይነት ያገኘ ቢሆንም ሀሳብን በነጻ የመግለጽና የነጻ ፕሬስ መብት በተለይ በታዳጊ ሀገራት ውስጥ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ሆኖ አይገኝም። ይታፈናል፡ ይገደባል። የመንግሥትን ስህተት፡ በሙስና መጨማለቅ፤ የምርጫን ሂደት ማደናቀፍ፤ በፍርድ ሂደት ጣልቃ መግባት፤ የሕዝብን ሀብት መዝረፍ፤ በሥልጣን መባለግ፤ ብሔራዊ ጥቅምን ከባዕዳን ጋር በመመሳጠር ጉዳት ማድረስና በመስሉ ርዕሶች ለምሳሌ ሂስን ያዘለ ዘገባ የሚያቀርቡ ጋዜጠኞች ዛቻ፣ ክትትል፣ ዘብጢያ መወርወር አለፍ ካለም ለሕይወተ ሕልፈት መዳረግ የበርካታዎች እጣ ነው። ባብዛኛው ሀገራት ውስጥ የሚገኙ የዜና ተቋማት የመንግሥት ቁጥጥር ስለሚደረግባቸው በአሁኑ ወቅት በዓለም አቀፍ ደረጃ 1/3ኛ የሚሆነው የዓለም ህዝብ ነፃ የዜናና ፕሬስ አገልግሎት ተጠቃሚ ሊሆን አልቻለም። ለዚህም ነው ነጻ ፕሬስ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተከብሮ ተግባራዊ እንዲሆን፤ ለእስር ተዳርገው እንግልት ለሚደረሰባቸው ተፈትተው እርዳታም እንዲያገኙ ጥብቅና ለመቆም፤ ለሞት የተዳረጉትንና ደብዛቸው የጠፋውን ደግሞ ለመዘከር እንዲያስችል ዩኔስኮ በ1991 (እ.አ.አ) ባቀረበው ሃሳብ መሠረት የተ.መ.ድርጅት በ1993 (እ.አ.አ) ጠቅላላ ስብሰባው ሚያዝያ 25 (ሜይ 3) ቀንን 'ዓለም አቀፍ የፕሬስ ነፃነት ቀን' ብሎ እንዲከበር በወሰነው መሰረት ይኸው በያመቱ እኛም የማንነታችን መግለጫ ከሆኑት ውስጥ አንዱ ነውና እንዘከረዋለን።

ባለፉት 25 አመታት የፕሬስ ነፃነት በብዙ ሀገራት እየተከበረ መገኘቱን ጥናቶች ይጠቁማሉ። በ1984 ዓ.ም (እ.አ.አ) በዓለም አቀፍ ደረጃ 23 በመቶ የሚሆኑት የነፃ ፕሬስ አገልግሎት ተጠቃሚ ነበሩ። ይህ አሃዝ በ2007 ዓ.ም (እ.አ.አ) ወደ 38 በመቶ ከፍ ሊል ቢችልም ባለፉት ከሰባት እስከ አሥር አመታት ውስጥ ወደ 36 በመቶ ወርዶ ይገኛል። ይህ ሁናቴ ጨርሶ ወደታች እንዳያቆለቁል ደግሞ ከፍተኛ ሥጋት መስፈኑን በጋዜጠኞች ላይ እየደረሱ ያሉትን ወከባዎች ዋቢ በማድረግ እየተገለጸ ይገኛል። በ2009 ዓ.ም (እ.አ.አ) ፍሪደም ሃውስ የተባለ ተቋም ባቀረበው ጥናታዊ ዘገባ ውስጥ እንደተገለጸው በወያኔ አገዛዝ ሥር ያለችው ኢትዮጵያ ለምሳሌ፣ መጠነ ሰፊ የሆነ ፕሮፓጋንዳ ቢደረግም ከ195 ሀገራት ውስጥ 165ኛ መውጣቷ ብቻ ሳይሆን የፕሬስ ነፃነት የሌላት ሀገር ተደርጋም ተፈርጃለች። የድንበር የለሽ ጋዜጠኞች ተቋምም በበኩሉ ተመሳሳይ ውጤት ያለው ዘገባ አቅርቧል። ለጋዜጠኞች ጥብቅና የቆመው ተቋምም ከሦስት ዓመት በፊት መለስ ዜናዊን ከአሥሩ የነጻ ፕሬስ ጠላቶች መካከል አንደኛው መሆኑን አብስሮ እንደነበር የሚታወስ ነው።

ወያኔ የነፃ ፕሬስ ጠላትነቱን ያረጋገጠው ሥልጣን እንደጨበጠ በመሆኑ ላለፉት 18 አመታት አንድን አፋኝ ሕግ በሌላ አፋኝ ህግ እየተካና እያጠናከረ የነፃ ፕሬስ አባላትን ማዋከቢና በተለይም ራሳቸው በራሳቸው ላይ ቁጥጥር እንዲያደርጉ - ይህንን ባሡፍር እንዴት ይተረጎምብኝ ይሆን? ምንስ ይደርስብኝ ይሆን? እያለ እንዲጨነቅ - የሚያስገድድ የፖለቲካ ሥርዓት ያሰፈነ፤ በኢትዮጵያ ላይ የመጣ መቅሰፍት ነው። ወያኔ በፈለገው መልክ ሊተረጉመው በሚችለው አንቀጽ ጋዜጠኞችን እያስፈራራና እያዋከበ ሀሳብን በነጻ የመግለጽ ነፃነት መብትን ይኸው እስካሁን ድረስ እንዳፈነ ይገኛል። ወያኔ ሥልጣን ከያዘበት ጊዜ አንስቶ በኢትዮጵያ ለታሰሩ፥ ለተገደሉ፥ ለስደት ለተዳረጉ በርካታ ጋዜጠኞች ዋና ተጠያቂ ነው። የእስራት ፍርድ ተፈርዶባቸው በመማቀቅ ላይ የሚገኙ አሁንም በርካታ ናቸው። የተወሰኑት ደግሞ እንደ ኲምሳ በራዩ፥ ብርሃኑ እጅጉና ሌሎችም ደብዛቸው እንዲጠፋ ተደርገዋል።

በቅርቡ እንኳን መለስ ዜናዊ ወያኔ ምንም አይነት ማስረጃ ሳያቀርብ ጋዜጠኞችን በደፈናው ከተቃዋሚዎች ጋር በመመሳጠር አገዛዙን ለማስወገድ ሁከትና ቅስቀሳ እያደረጉብኝ ናቸው በማለት እየከሰሰ የፍርሃት ሰቀቀን በሕዝቡ ውስጥ ለማሰራጨት እየጣረ ይገኛል። ይህ ብቻ አይደለም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለ ሀገሩ በመጠኑም ቢሆን ዜናዎች ሊከታተል የሚችልባቸውን የሬዲዮ ስርጭቶች እንዳይደመጡ ለማድረግ ባለው አቅም ሁሉ በመጣር ላይ ነው። ይህንን ዘዴ በተለይ በምርጫ ወቅት በስፋት እየተገለገለበት መሆኑ ደግሞ ያለምክንያት አይደለም። የሬዲዮ ስርጭቶቹ በተደጋጋሚ ክሶች እያቀረቡበት ያለ ቢሆንም ራሱ መለስ ዜናውም እብሪት በተቀላቀለበት ሁኔታ ስርጭቶቹን ከማፈን (ጃም ከማስደረግ) የሚያግደው ምንም ነገር እንደሌለ በአደባባይ መግለጹ የነጻ ፕሬስ ጠላትነቱን የሚያረጋግጥ እንደሆነ ግልጽ ነው። በበርካታ ዜጎቻችን ዘንድ ከፍተኛ አድናቆትንና ከበሬታን በማስገኘት ላይ የሚገኘው ፍኖተ ዴሞክራሲና አንድ የባዕድ የሬድዮ ስርጭት የዚሁ የአፈናው ሰለባ መሆናቸው ያወጧቸው የተቃውሞ መግለጫዎቻቸው ያረጋግጣሉ። የዜናና የሀሳብ ልውውጦች በሕዝቡ መካከል እንዳይኖር ድሪ ግጾች እንዳይነበቡ እያደረገ ያለው የዚሁ ነጸብራቅ ነው። ተመሳሳይ ላባ ያላቸው ወፎች አብረው ይበራሉ ነውና በፀረ ነፃ ፕሬስ ድርጊቶቻቸው የሚወገዙ ባዕዳኖችም እየተባበሯቸው ይገኛሉ።

በአሁኑ ወቅት ወያኔ በሕዝብ ሃብት የሚንቀሳቀሱትን የዜና ተቋማት በሙሉ በሱ ቁጥጥር በማድረግና ሌሎች በራሳቸው ጥረት ለመንቀሳቀስ የሚጥሩትን ጋዜጠኞች ደግሞ በአፈና ሕግ አስሮና ገድቦ ይዞ በወያኔ አሸናፊነት ስለሚደመደመው የምርጫ ተውኔት እንኳ እንዳይጋለጥ በመፍራት ሕዝቡን የማወቅ መብቱን



EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France

ነፍጎታል። ባሁኑ ጊዜ ጋዜጠኞችን እየተጠቀመባቸው ያለው፣ የተቃዋሚው አባላት በሕዝባዊ ስብሰባ የሚሰጧቸውን ገለጻዎች ለመቅዳትና ለስለላ ተግባርና ብሎም ተቃዋሚዎችን በመክሰስ በፍርድ ቤት ለማስቀጣት ይቻለው ዘንድ መሆኑ ደግሞ በአደባባይ በግልጽ የተነገረ ነውና ምስጢር አይደለም። ለዚህም ነው ነፃ ፕሬስ በሌለበት ፍትሃዊ ምርጫ የሚሉት ነገር ሊኖር አይችልም ተብሎ ሀሳብን በነጻ የመግለጽ መብት እንዲከበር አበክሮ እየተጠየቀ የሚገኘው። ይህ መሠረታዊ የሆነው መብት ደግሞ ለብቻው እንዲነጠል ተደርጎ ተግባራዊ የሚሆን ሳይሆን ከሌሎች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች፣ ከሕግ የበላይነት፣ ከዴሞክራሲያዊ አስተዳደር መገኘት ጋር በጥብቅ የተሳሰረ በመሆኑ የጥያቄውን ክብደት ያጎላዋል። ለዚህም ነው የዴሞክራሲ ትግሉን ከነጻ ፕሬስ ጋር በማያያዝ ትንቅንቁ እስካሁን ድረስ ቀጣይ ሆኖ የሚገኘው።

ወያኔዎች የነፃ ፕሬስ ሕግን በሕገ አገዛዛቸው አስፍረናል በማለት ቢመጻደቁም ሕጋቸው ዳዴ ለማለት የሚፍጨረጨሩትን የነጻው ፕሬስ አባላትን ከሞት፤ ከእስራትና ከስደት ከለላ ሊሆን ቀርቶ የተጻፈበትን ወረቀት ያህል እንኳን ክብደት የሌለው መሆኑ በተግባር ታይቷል። ስለዚህም ወያኔና የሱ ደጋፊዎች ሀሳብን በነፃ የመግለጽ መብትን ለመጎናፀፍ የኢትዮጵያ ሕዝብ የከፈላቸውን የሕይወት ዋጋ እንደሌሉ አድርገው እንደፈለጉት ሊፈነጩ ሊፈቀድላቸው ጨርሶ አይገባም። ሕዝብ በተራ ፕሮፓጋንዳ የሚታለል አለመሆኑን በተግባር፣ በትግል እንዲጋቱት ማድረግ ደግሞ የማይሸሹት ሀገራዊ ግዳጅ ነው። ወያኔና ደጋፊዎቹ በሕዝብ ሕሊና ያደረሱት ቁስል ደርቆ ጠባሳ አላወጣምና ደረቅ እንጨት እየሰደዱ ሀዘኑን የከበደ ለማድረግ ቢፍጨረጨሩም ሕዝብ በዚህ ድርጊታቸው ተደናግጦ የጀመረውን የነጻነት ትግሉን አያቆምም፤ እንዲያውም በጠነከረ ትግል ወደፊት እስከ ድሉ ድረስ ይጓዛል እንጂ! ይህ ቀን በሚዘከርበት ወቅት ታሳቢ የሚሆነው ይህ ብቻ ነው።

ወያኔ ነፃ ፕሬስን የሚፈራው አለምክንያት አይደለም። በኢትዮጵያ ሕዝብ ፊት አምባገነንነቱንና የጥፋት ተልዕኮ ሚናውን አጋልጠው በሕዝብ እንዲተፉ ማድረጋቸውን በሚገባ ስለሚያውቅ ብቻ ነው። ይህም ብቻ አይደለም። በዚህ ጥረታቸው ከቀጠሉ ወያኔን ከሥልጣን ለማስወገድ በሚደረገው ሕዝባዊ ትግል የሚያበረክቱት አስተዋፅዖ ከፍተኛ መሆኑን በማወቁ ጭምር ነው። በኛ በኩል ግን ይህ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ደግሞ ጽኑ ፍላጎታችንና ለስኬታማነቱም ጠንክረን የምንንቀሳቀስበት ይሆናል። በዚህ በኩል ደግሞ ሕዝባችን ከጎናችን ለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለንም።

በሀገራችን ለነጻው ፕሬስ ማደግና መጎልበት ከልብ ቀና አመለካከት ያላቸው ኢትዮጵያዊያን ሀገር ወዳድ ሁሉ በዚህ ዛሬ በሚያከብሩት ዓለም አቀፍ የፕሬስ ነፃነት ቀን፣ በነፃ ፕሬስ አባላት ላይ እያደረሰ ያለውን የማናህሎኝነትና የማንአለብኝነት ተግባር ማውገዝና፣ ጸረ ነፃ ፕሬስ የሆኑ ሕጎች ተሰርዘው ሕዝብ የማወቅ መብቱ እንዲከበር የጋራ ክንዳቸውን ማስተባበር ሃላፊነታቸው ግዴታቸውም ነው የሚል ፅኑ እምነት አለን። ኢሕአፓ ይህንን የነፃ ፕሬስ ቀን ሲያከብርና ሲዘከር ለነፃ ፕሬስ አባላት ያለውን አድናቆትና ክብር እየገለጸ ነውና በተቻለው አቅም ሁሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሀሳቡን በነጻ ለመግለጽ ያለው ተፈጥሯዊ መብት እንዲከበርለት የሚያደርገውን ትግል አጠናክሮ ይቀጥልበታል። ሀገር ወዳድ የሆኑ ኃይሎችም በበኩላቸው በዚህ ቀና ጎዳና የነጻ ፕሬስ አባላትን እንዲተባበሯቸው ዳግም ጥሪውን ያስተላልፋሉ።

ሀሳብን በነጻ የመግለጽ መብት ያለገደብ ይከበር!!



EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel . 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com

Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France